# በእርግጥስ ምዕራባውያን የዓለም ህዝቦች ነፃነታችውን ቢቀዳጁና ዲሞክራሲን ቢያሰፍኑ ደስተኛ ይሆናሉ ወይ ? ለዶክተር ብርሃኑ ነጋ ዳላስ ከተማ ለኢትዮጵያውያን ላቀረበው ሀተታ መልስ!

ዶክተር ብርሃኑ ነጋ ከምርጫ 1997 ዓ.ም ወዲህ ታዋቂ እየሆነ የመጣና ፣ በተለይም እስር ቤት ውስጥ ሆኖ መጽሀፍ ለማሳተም በመብቃቱ በብዙ ኢትዮጵያውያን ዘንድ ተቀባይነትን አግኝቷል። ከዚህም በላይ እሱ በሚቆጣጠረው ኢሳት የሚባለው የቴሌቪዥን ጣቢያ ላይ እየተጋበዘ የሚሰጠው የቃለ-መጠይቅ ምልልስ ብዙ ዝናን አትርፎለታል። በተጨማሪም በአውሮፓው አንድነትና በአሜሪካኖች የሚታወቅ ነው። እሱም በአሜሪካን የኮርፖሬት ዲሞክራሲ የሚያምንና ከእስር ቤት ከወጣና አሜሪካ ከተመለሰ በኋላ አንድ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ባደረገው ንግግር ***„ለምን እንደሆን አላውቅም የኢትዮጵያ ህዝብ አሜሪካንን ከልቡ ይወዳል“*** በማለት የራሱን ውስጣዊ ፊላጎት በግልጽ ተናግሯል። ከዚህ በመነሳት የሱን የትግል ስልትና የሚሰጣቸውን ትንተናዎች የሚከታተል ሁሉ ፣ ትንተናዎቹ የቱን ያህል ዕውነተኛውን የነጻነት ፊለግ የሚከተል መሆኑንና አለመሆኑን ፣ ዲሞክራሲያዊ አስተሳሰቡም የቱን ያህል ለኢትዮጵያ ህዝብ ዕውነተኛውን ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ለመገንባት ያስችለው አያስችለው ፣ እስካሁን ድረስ ለውይይት ቀርቦ ክርክር አልተደረገበትም። እንዲያው በደፈናው ሁሉም ካለምንም ውጣ ውረድ ዝም ብሎ ዐይኑን ጨፍኖ እንዲቀበልና እንዲያምን ሆኗል።

ከሁለት ሳምንት በፊት የቱኒዚያውን ህዝባዊ እንቅስቃሴና የቤን ዓሊን ከስልጣን መባረር አስታኮ ርስ በርሱ የሚቃረን መግለጫ ከግንቦት ሰባት ተሰጥቷል። በመግለጫውም መሰረት ፣ እስካሁን ድረስ የቤን ዓሊን አገዛዝ በምዕራቦች ፣ በተለይም በአሜሪካኖች ይደገፍ እንደነበር ፣ አሁን ደግሞ እንደተፉት ያብራራል። በግንቦት ሰባት መሪዎች አስተሳሰብና ዕምነት ይህ ዐይነቱ አምባገነኖችን የመደገፉና የማስታጠቁ ጉዳይ ኖርማል እንደሆነና ምዕራቦችም የአገዛዙ ፀረ-ዲሞክራሲ ተግባርና ህዝብን ማፈን ተባባሪ እንዳልሆኑ ተቀመጧል። ስለሆነም ይላል ፣ ከኛ የሚጠበቀው ተጠናክሮ መገኘትና ምዕራቦችን ወደኛ ጎን እንዲቆሙ ማድረግ ነው ይለናል። ይህንን በሚመለከት ማብራሪያ እንዲሰጠኝ ብጠይቅም እስካሁን ድረስ አናዳችም መልስ አላገኘሁም። ውድ አንባቢያን ለፍትህና ለዲሞክራሲ እንዲሁም ለነጻነት እታገላለሁ ከሚል ድርጅት መልስ ሲታጣ ምን ይባላል? በእኔ ዕምነት ዲሞክራት ነኝ የሚል ድርጅትም ሆነ ግለሰብ ለሚቀርብለት ጥያቄ መልስ መስጠት መቻል አለበት። ግዴታውም ነው። መልስ ለመስጠት ዝግጁ ያልሆነ ድርጅት ደግሞ ዲሞክራት ነኝ ብሎ ሊመጻደቅና ተዝናንቶ ሊቀመጥ አይችልም። በአንድ ህዝብ ስምም እየማለና እየተገዘተ ነጻ ላወጣችሁ ነው እያለ የትግሉን ሜዳ የማጥበብ መብት የለውም። ህዝብን ማሳሳት የለበትም።

አሁን በቅርቡ ዳላስ ከተማ ላይ ዶክተር ብርሃኑ ነጋ ለሁለት መቶ ያህል ኢትዮጵያውያን ባደረገው ንግግር ልክ ግንቦት ሰባት ላይ የተሰጠውን ዐይነት መግልጫ የሚመስል ሀተታ አቅርቧል። በዶክተር ብርሃኑ አገላለጽም “ ***ምዕራባውያን የዓለም ህዝቦች ነፃነታቸውን ቢቀዳጁ እና ዲሞክራሲን ቢያሰፍኑ ደስተኞች ይሆናሉ“*** ይለናል። በመቀጠልም ፣ ***„ሆኖም ግን ከሌሎች አገራት ህዝቦች ነፃነት የራሳቸውን ደህንነት ያስቀድማሉ።“*** በማለት የእቅጩን ይነግረናል። ይቀጥልና *„ለነፃነታችን በምናደርገው ትግል የዲሞክራሲያዊ አገሮች ድጋፍ ለማግኘት መሬት ላይ ያለው ሁኔታ መቀየር እንዳለበት ቱኒዚያም ግብጽም አረጋግጠውልናል“* በማለት አዲስ ቲዎሪና ታሪክ ያስተምረናል።

በሌላ ወገን ደግሞ ዶክተር በርሃኑ እንደሚለንና ሁላችንም እንደምናውቀው ፣ አብዛኛዎቹ እነዚህ ጨቋኝና አምባገነን መንግስታት የፀረ-ሽበርተኝነት አጋዥ ስለሆኑ ከአሜሪካም ሆነ ከተቀረው የምዕራብ አውሮፓ መንግስታት ጋር በጥብቅ መስራታቸው ብቻ ሳይሆን ህዝባቸውን ለመጨቆን የሚያገለግላቸውን የጭቆና መሳሪያዎች ከአሜሪካን ያገኙ

እንደነበር በግልጽ ያትታል። በገጽ አራት ላይ ፣ *„ እነዚህ አገሮች በፀረ-ሽብር ትግል የአሜሪካና የአውሮፓ መንግስታት አገሮች አጋሮች የሆኑ ፣ በዚህም ምክንያት የአሜሪካና የአውሮፓ መንግስታት እንክብካቤና ጥበቃ ያልተለያቸው ናቸው ። በተለይም ሙባራክ የአሜሪካ ሁነኛ ወዳጅ መሆኑ የአሜሪካ ከፍተኛ ድጋፍ ሲያገኝ የነበር ከግብጽ ይልቅ ለአሜሪካ ጥቅም የቆመ ሰው ነበር።“* በማለት አቅጩን ይነግረናል። እዚህ ላይ መነሳት ያለበት ጥያቄ አሜሪካንም ሆነ የምዕራብ አውሮፓ አገሮች ሌሎች አገሮች ዲሞክራሲያዊ ስርዓት እንዲኖራቸውና ነጻ እንዲሆኑ ከፈለጉ ለምንስ እነዚህን ከመሳሰሉት ዲሞክራሲን ከሚያፍኑና የተስተካከለ ዕድገት እንዳይኖር ህዝባችውን አረግጠው ከያዙ ጋር የፀረ-ሽብርተኛ አጋዥ ስለሆኑ ብቻ አብረው መስራት እንደተገደዱ ነው ? በነዚህ አገሮች ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ቢኖርና ህዝቦቻቸውም የተደላደለ ኑሮ ቢኖሩ ኑሮ ሽብርተኝነትን ለመቋቋም ይኸኛው ቀናው መንገድ የተሻለ አይሆንም ነበር ወይ? በህብረተሰብ ሳይንስ እንደሚታወቀው አንድ ህብረተሰብ ሁሉ ነገር ከዘጋጀለት ፣ የስራ መስክ በበቂው ከተከፈተለት ፣ ዲሞክራሲያዊ ተሳትፎ ኖሮት ሃሳቡን መግልጽ የሚችልና በአገር ግንባታ ውስጥ በቀጥታ የሚሳተፍ ከሆነ ወደ ሌላ መጥፎ ተግባር እንደማያመራ ነው። ታዲያ በሳይንስና በቴክኖሎጂ እንዲሁም በልዩ ልዩ የምሁር ችሎታ ቀድመውና ተራቀው የሄዱት አሜሪካና የምዕራብ አውሮፓ አገሮች በእንደዚህ ዐይነቱ ህዝብን አደንቁሮና አድኽይቶ በሚያስቀር ተግባር ውስጥ ምን አሳተፋቸው? አንድ አገርስ ደኽይቶና ተዳክሞ ቢኖር ምን ጥቅም ያገኛሉ? ከኢኮኖሚ ስሌትስ አንፃር የአንድ አገር ህዝብ የመግዛት ኃይሉ ጠንካራና የውጭን አገር ምርት ገዝቶ ለመጠቀም የሚችለው የህበረተሰብ ክፍል ሰፋ ያለ ከሆነ አሜሪካንም ሆነ የምዕራብ አውሮፓ አገሮች ለዕቃዎቻቸው ሰፊ ገበያ አያገኙም ወይ? አንድ አገርስ የኛን ጥቅም ታስጠብቃለች ሲሉ ምን ማለታቸው ነው? እንደዚህ ዐይነቱ የአሜሪካንም ሆነ የምዕራብ አውሮፓ አገሮች ከአምባገነን መንግስታት ጋር እጅና ጓንቲ ሆኖ አብሮ መስራት አንድን አገር ከማዳከምና ከማደኽይት ስትራቴጂ አንፃር ተነጥሎ ሊታይ ይችላል ወይ? እነዚህን የመሳሰሉት አገሮች ጥሩ ድጋፍ ቢያገኙና ኢኮኖሚያቸውም ቢያድግ ወደ ፊት እንደ ጃፓን ፣ ደቡብ ኮሪያ ዛሬ ደግሞ ቻይና ሌላ ተቀናቃኝ አገሮች ሊነሱብን ይችሉ ይሆናል ብለው በመገመት አይደለም ወይ ድርጊታቸውን ወደ ጦርነትና ወደ ሌላ የህዝቦቻቸውን አስተሳሰብ ወደሚበታትን አቅጣጫ የሚመሩት? እንደዚህ ዐይነቱንስ አሳሳች ፖለቲካ መከትል የአሜሪካንና የምዕራብ አውሮፓ ዋናው ስትራቴጂያቸው አይደለም ወይ? ዶክተር ብርሃኑ ነጋ እነዚህን የመሳሰሉትን ጥያቄዎች አንስቶ ቢያነጋግረንና ቢያወያየን ኖሮ ለትግላችን ስልት የሚሆነን መንደርደሪያ ሊሰጠን ይችል ነበር ብዬ አምናለሁ። ይሁንና አንድም ቦታ ላይ ማብራሪ አልሰጠም።

ወደ መሰረተ-ሃሳቡ ስንመጣ የካፒታሊስት አገሮች የዓለም ህዝብ ዲሞክራሲን ቢጎናጸፉና ነጻነትን ቢቀዳጁ ደስታውን አይችሉትም የሚለው ፣ ምን ዐይነት ዲሞክራሲን እንደሚመኙልን ግልጽ አድርጎ አላስቀመጠም። የነሱን ዐይነት ዲሞክራሲያዊ አስተዳደርን ነው የሚለን ከሆነ ደግሞ ዲሞክራሲያዊ አስተዳደራቸው እንዲሁ በፎርማል ደረጃ የሚገለጽ ቢሆንም የምዕራቡ ዲሞክራሲ የተወሰነ የህብረተሰብን ግኑኝነትና የኃይሎችን አሰላለፍ የሚገልጽ ነው። ዲሞክራሲውም ቀጥተኛ ተሳትፎ የሌለበት የውክልና ዲሞክራሲ ነው። ልክ አስራስምንት ዐመት ዕድሜ ያልሞላው ወጣት በምርጫ ጊዜ ድምጽ በመስጠት መሳተፍ እንዳማይችል ሁሉ የውክልና ዲሞክራሲ ተመርጠናል ፣ የፈለግነውን ማድረግ እንችላለን በሚሉ ተማረጮች እጅግ በረቀቀ ሁኔታ ማንኛውም ነገር በመራጩ ህዝብ ላይ የሚጫንበትና እንዲቀበለው የሚደረግ ነው። እንደሚታወቀው ይህ ዐይነቱ የፓርሊሜንታሪ ዲሞክራሲ በታሪክ ውስጥ ሌሎች አማራጭ ዲሞክራሲያዊ ስርዓቶችን እየተቀናቀነ በመውጣት የከበርቴውን መደብ የበላይነት ለማረጋገጥ የታቸለበትና በመሰረቱ እንደ ግል ሀብት የመሳስሉትን ህጋዊ በማድረግ ህብረተሰቡ ይህንን አምኖ እንዲቀበል የተደረገበት ነው። የምዕራቡ ካፒታሊስት ዲሞክራሲ የዛሬው የዕደገት ደረጃ ሊደርስ የቻለው እየወደቀና እየተነሳ ፣ በተለያዩ ኃይሎች መሀከል በሃሳብም ሆነ በጉልበት ግብግብ ከተፈጠረና ቀስ በቀስ ህብረተስብአዊ መረጋጋት ከተፈጠረ በኋላ ነው። ለዚህ ደግሞ ከ13ኛው ክፍለ-ዘመን ጀምሮ ቀስ በቀስ በፍልስፍና ላይ የተመሰረተ ጭንቅላትን ለአዳዲስ

አስተሳስቦች ክፍት ያደረገ አስተሳሰብ በተለይም በሰው ልጅ ሚና ላይ ያተኮረና በሰው ልጅና በተፈጥሮ መሀከል ያለውን ግኑኝነት የሚመረምር ሰፋ ያለ ምሁራዊ እንቅስቃሴ በመካሄዱም ጭምር ነው። በተለይም በሬናሳንስ አማካይነት የተፈጠረው ከተማዎችን መገንባት ፣ የንግድ ተግባር ከዕደ-ጥበብ ጋር በማያያዝ የህብረተሰቡን አትኮሮ መሰብሰብና ጥልቀት እንዲኖረው ማድረግ ፣ ይህንን ከጥንታዊ ሙዚቃና ስዕል ጋር በማገናኘት ወደ ህብረ-ብሄር ግንባታ ለመሸጋገር የተቻለበት ነው። ይሁንና ግን ይህ ዐይነቱ የውጣ ውረድ ጉዞ ዕውነተኛውን በስብአዊነት ላይ የተመረኮዘውን ዲሞክራሲያዊ ስርዓትም እየተቀናቀነ እንደመጣ መገንዘብ ይቻላል። በተለይም የኢምፐሪሲስቶች የነጻ ገበያና የነጻ ንግድ እንደ ዋና የኢኮኖሚ ግንባታ መርሆች ሆነው ተቀባይነት እንዲኖራቸው ከተደረጉ ወዲህ የፎርማል ዲሞክራሲ በብዙ የአውሮፓ አገሮች ተቀባይነትን እያገኘና ብዙ ነገሮችን እያጣመመ ለመምጣት ችሏል። በሌላ አነጋገር የዛሬው የከብርቴው ዲሞክራሲ በአንድ ኃይል ችሮታ የተገኘ ሳይሆን የትግል ውጤት ቢሆንም የኋላ ኋላ ግን ባህርዩን ሊለውጥ ችሏል። በመጀመሪያ ግን መሰረቱ በራሱ በከበርቴው መደብና በመንግስት የተነጠፈ ሳይሆን ለለውጥ በሚታገሉ በተለያዩ ምሁራን አማካይነት ነው። የከበርቴው መደብ ግን የፊዩዳሉን መደብና አሪስትክራሲውን ለመዋጋት ሲል የግንባር ቀደምትነት ሚና በመውሰድ ኢንስቲቱሽናዊ ሪፎርሞች ማድረግ ጀመረ። ይህ ዐይነቱ ዲሞክራሲ ተቀባይነትን ካገኘም በኋላ በተለይም የኢኮኖሚ ኤጀንቶች ርስ በራሳቸው በሚያደርጉት ትግልና በመንግስቱም መኪና ላይ በሚያካሄድት ተፅዕኖ ባህርዩን እየለወጠ ሊመጣ ችሏል። ህግን የሚያረቀውና ህግን ተግባራዊ የሚያደርጉት ሙሉ በሙሉ በሎቢስቶች የተገሰገሱና ለራሳቸው በሚስማማ መልክ ህግንም ለማውጣት የደረሱበት ደረጃ እንዳለ ሁኔታዎችን ለሚከታተል ግልጽ ነው። በዘመነ ኒዎ-ሊበራሊዝምና በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዘመንም የፓርሊሜንታሪ ዲሞክራሲ ውስንነቱን እያረጋገጠ ነው። ይህም ማለት የሰው ልጅ ነጻነት በከፍተኛ ደረጃ በጥያቄ ውስጥ እየገባና የተለያዩ ምክንያቶችን እያሳበቡ ዲሞክራሲያዊ መብቶች እየተሸረሸሩ በመምጣት ላይ ናቸው።

የፓርቲዎችን አደረጃጀትና የፖለቲካ መስመር ስንመለከት ደግሞ ፣ በተለይ የሊበራል ዲሞክራቲክ ፓርቲዎችና የክርስቲያን ዲሞክራቲክ ፓርቲዎች እንደስማቸው ሳይሆን በአማዛኙ ኢኮኖሚውን የሚቆጣጠረውን የህብረተሰብ ክፍል ጥቅም ነው የሚያስጠብቁት። ለምሳሌ የሊበራል ዲሞክራቲክ ፓርቲዎች ሜዳው ነጻ ነው ፣ ማንም ሰው እንደችሎታው መታገል ይቻላል ፣ እንደአስተዋጽዖም ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ያገኛል ቢሉና ቢሰብኩም ፣ የኢኮኖሚው ሜዳ እነሱ እንደሚሉት ክፍት አይደለም። አንድ ሰው ሊሰራ የሚችለው ስራ ሲያገኝ ብቻ ነው። ሁለተኛ ፣ በሚያወጡት የኢኮኖሚ ፖሊሲ አብዛኛውን ጊዜ የኢንዱስትሪና የፊናንስ ኦሊጋርኪዎችን ጥቅም አጉልቶ የሚያሳይና ተግባራዊ የሚያደርግ ነው። ለምሳሌ በቀረጥ ቅነሳ ፖሊሲ አማካይነትና በድጎማ መቀነስ ሀብት ከታች ወደ ላይ እንዲሸጋሸግ በማድረግ ሰፊውን ህዝብ ወደ ድህነት ይገፈትራሉ። እንደዚሁም የክርስቲያን ዲሞክራቲክ ፓርቲዎች እንደስማቸው እኩልነትና ሰብአዊነትን የሚያራምዱ ሳይሆን በስሙ በመነገድ እኩልነት እንዳይኖር እገዳ የሚያደርጉ ናቸው። እነሱም ልክ እንደ ሊበራል ዲሞክራቶች በቀረጥና በተለያዩ የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች የሀብት ክፍፍል እንዲዛባ በማድረግ የሰፊውን ህዝብ ሞራል እያዳከሙ ነው። በተለይም በትምህርት ፖሊሲ ላይ የሚያካሂዱት ግልጽና አድልዎ የተሞላበት ፖሊሲ የታችኛው የህብረተሰብ ክፍል ጥሩ ቦታ እንዳይኖረው እያደረጉ ነው። ለምሳሌ ወጣቶች ከአንደኛ ክፍል ጀምሮ እስከስድስተኛ ወይም እስከ አስረኛ ክፍል ድረስ የመማር ዕድል የላቸውም። ከሰራተኛው የህብረተስብ ክፍል የመጡ ስድስተኛ ክፍል ከደረሱ በኋላ በመጣራት ወደ ታች ቀጭጨው እንዲቀሩ ይገደዳሉ። እንክብካቤ ማግኘት የሚችሉ ህጻናት እስከ ዩኒቨርሲቲ ድረስ የመውጣት ዕድል አላቸው። የስራ ዕድልና የማኔጅር ፖስት ማግኘት የሚችሉት ከሰራተኛው ህብረተስብ የፈለቁ ሳይሆኑ ፣ ከላይኛው ህብረተስብ ክፍል የመጡ ናቸው። በቅርቡ በሰፊ ተመርምሮ በወጣ መጽሀፍ ህብረተሰቡ በጠበቀ ሂራርኪ የተደራጀ ስለሆነ ከፍተኛ ትምህርት ተምሮ ጥሩ ስራ ሊያገኝ የሚችለው ከከብርቴው ፣ ከጠበቃና ጥሩ ገቢ አላቸው ከሚባሉ የህብረተሰብ ክፍሎች ብቻ ነው። በሌላ ጥናት ደግሞ ፣ ፓርቲዎች ከውጭ ሆነው በተደራጁ ጠበቃዎችና የኢኮኖሚክስ አማካሪዎች የተተበተቡ ሲሆን ፣ አማካሪዎቹም የተወሳሰበ ሞዴል በማውጣት የቱን ያህል ሀብት ያለውን እንደገና ሀብታም እንደሚያደርጉት ነው። አሜሪካ ደግሞ ከዚህ

የባሰ ነው። የኮርፖሬቶች ጥቅም በከፍተኛ ደረጃ ተግባራዊ የሚደረግበትና ሁለቱም ፓርቲዎች ካለኮርፖሬቶች ፍላጎት አንድም ሜትር ፈቀቅ ማለት አይችሉም። ሰሞኑን በቀረበ ስፊ የሬዲዮ ሀተታ እያንዳንዱ ፓርሊሜንቴሪያን ለምሳ ወደ ምግብ ቤት በሚሄድበት ጊዜ ለምግብና ለመጠጥ መክፈል እንደሌለበትና፣ ቢሉም ቀድሞ ተከፍሎ እንደሚጠብቀው ነው። በሀተታውም መሰረት ጋባዦቹ ሄጅ ፈንድስ፣ ኢንቬስትሜንት ባንኮችና የዎል ስትሪት ማኔጀሮች ናችው። ለእያንዳንዱ ፓርሊሜንቴሪያን እስከ ዘጠና ዶላር ድረስ ወጪ ይደረግለታል። ሀቁ ይህ ሆኖ ሳለ አንዳንድ ኢትዮጵያውያን ሊነግሩን እንደሚፈልጉት ፓርቲዎቹ ከአድለዎ ነጻ የሆኑ አይደሉም። እንደዚህ ዐይነቱ የሎቢስቶች ስራ ዓለም አቀፋዊ ባህርይ ይዞ በመምጣትና የሶስተኛውን ዓለም አገሮች ኤሊትን እየተበተበ በመምጣት ለዕድገትና ለዲሞክራሲ ማበብ እንቀፋት በመሆን ላይ ነው። በተለይም በአሁኑ ወቅት የፊናንስ ካፒታል እጅግ በጠናከረበት ጊዜና ከሚሊታሪና ከኢንዱስትሪ ኮምፕሌክስ ጋር በተሳሰረበት ወቅት የሶስተኛ ዓለም መንግስታት መሪዎች በልዩ ልዩ ጥቅሞች በመታሰር የዚህ ዐይነቱ የአገዛዝ ሰንሰለት አካል በመሆንና ጦርነትን ፈልፋይ እንዲሆኑ በመገደድ ለሰላምና ለዕድገት ዕንቅፋት ሆነዋል። ከዚህ ስንነሳ ዶክተር ብርሃኑ ምን ዐይነት የሊበራል ዲሞክራሲና የኢኮኖሚ ፖሊሲ ለማራመድ እንደሚፈልግና ምን ዐይነትስ ዕርዳታ ከምዕራቦች ማግኘት እንደሚችልና እንደሚጠብቅ ግልጽ አድርጎ አላስቀመጠም።

በአገሮች መሀከል የተደረገውን ፍክክርና ተንኮል ስንመለከትም በመሀከላቸው መደጋገፍና መረዳዳት እንዳልነበረ መገንዘብ እንችላለን። በምዕራቡ ካፒታሊስት የትግል ታሪክ ውስጥ ቀድሞ የሄደው አንደኛው አገር በሌላው ላይ የራሱን የበላይነት ለማስፈን ትግልም ያካሄድ ነበር። በተለይም በሊበራል ዲሞክራሲ አስተሳሰብና በኢንዱስትሪ ግንባታ ቀድማ የሄደችው እንግሊዝ ሌሎች የምዕራብ አውሮፓ አገሮች የሷን ፈለግ እንዳይከተሉ አሻጥሮች ትሰራ ነበር። በተለይም የነጻ ንግድን ቲዎሪንና ዓለም አቀፋዊ የስራ ክፍፍልን በማዳበርና ተቀባይነት እንዲኖረው በማድረግ ሌሎች አገሮች በእርሻ ምርትና በሌሎች ጥሬ ሀብቶች ላይ ብቻ እንዲያተኩሩ የዕድገታቸውን አቅጣጫ ለማዛነፍ የማታደርገው ጥረት አልነበረም። በተለይም በጀርመን በኩል የፍልስፍና እንቅስቃሴ እያየለ በመምጣቱ የእንግሊዙን የኢምፐሪሲስቶች መንገድ እስከተወሰነም ደርጃ መቋቋም ተችሏል። እነላይብኒዝና በኋላ ደግሞ ፍሪድሪሽ ሊስት የእንግሊዙ የኢምፐሪሲስቶች ቲዎሪና የነጻ ንግድ ፍልስፍና እንዳይገባ አጥብቀው የታገሉና ለጀርመን ሳይንስና የኢኮኖሚ ዕድገት ከፍተኛ አስተዋጽዖ ያደረጉ ናቸው። ይህም ማለት በየአገሮች ውስጥ የተነጠፈው ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ከውስጥ የመጣና በትግል የተደረሰበት እንጂ አንድ በዕድገት ቀድሞ የሄደ አገር በሌሎችም ዲሞክራሲያዊ ስርዓት እንዲፈጠር ሰለፈለገና ለማገዝም ፈቃደኛ ስለሆነ አይደለም።

ወደ ኢትዮጵያና ወደተቀረው ሌላው የአፍሪቃ አገሮች ስንመጣ፣ የምዕራብ አውሮፓ የዲሞክራሲያዊ አጋዥነት በቀጥታ የራስን ጥቅም ከማስጠበቅና እነዚህን አገሮች ተቀጥያና ደካማ ሆነው እንዲቀሩ ከማድረግ ጋር በጥብቅ የተያያዘ ነው። ይህም ማለት በምዕራብ አውሮፓ የሚደገፈው የዲሞክራሲ ስርዓት አገነባብ ውስንነት ያለውና ወደ ዕውነተኛው ነጻነትም በፍጹም ሊያመራን አይችልም። ምክንያቱም ባለፉት ሰላሳ ዐመታት እንደተከታተልነው የምዕራቡ ካፒታሊስት ዲሞክራሲ ሲል ከኒዎ-ሊበራል አጀንዳ ጋር ስለሚያያይዝና በተወሰነ ኤሊት አማካይነት እሱ የሚፈልገውን ዲሞክራሲ ከበላይ ለመጫን ስለሚሻ ነው። ይህ ዐይነቱ ዲሞክራሲ ደግሞ ሰፊውን ህዝብ የሚያገልና የሳይንስና የቴክኖክሎጂን ተግባራዊነት የሚቀናቀን ነው። በዓለም አቀፍ ደረጃም የበላይነትን ለማስፍን የሚደረግ ትግል ስለሚካሄድ አሜሪካም ሆነ ሌሎች የምዕራብ አውሮፓ አገሮች በአፍሪካ ምድር ውስጥ ዕውነተኛ ዲሞክራሲያዊ ስርዓት እንዳይመሰረት የፈለጉትን ነገር ከማድረግ አይቆጠቡም። ሰለዚህም ምዕራብ አውሮፓውያንና አሜሪካ በአገራችን ምድር ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ቢሰፍን ደስታውን አይችሉትም የሚለው አባባል ከታሪክና ከህብረተሰብ ዕድገት ጋር እንዲሁም ከዓለም የፖለቲካ አወቃቀር ጋር እየተነፃፀረ የቀረበ አይደለም። የቀረውን ትተን፣ በተግባርም እንደታየውና በተለይም የስድሳ ዐመቱን የምዕራቡን ካፒታሊስት ዓለም፣ ዐለም አቀፋዊ ፖለቲካ ስንመለከት በአፍ ልፍፋና በተግባር መሀከል የምድርንና የሰማይን ያህል ልዩነት እንዳለ መገንዘብ ይቻላል።

ከ1945 ዓ.ም በኋላ የተፈጠረው አዲስ የኃይል አሰላለፍና የኢኮኖሚ አወቃቀር በተለይም አፍሪካውያንና ሌሎች የሶስተኛውን ዓለም አገሮች በኢንዱስትሪ እንዳያድጉና የሳይንስና የቴኮኖሎጂ ባለቤት እንዳይሆኑ ቆልፎ ይዟቸዋል። በተለይም ኢኮኖሚክስ ቲዎሪ ከአዲሱ የኃይል አሰላለፍ ጋር በማቀናጅት ብዙ የሶስተኛውን ዓለም ኤሊት ለማሳሳት ችለዋል። በቲዎሪዉም መሰረት የነጻ ንግድ የታሪክና የኃይል አሰላለፍ ለውጥ ውጤት ሳይሆን ተፈጥሮአዊና ማንኛውም አገር ተግባራዊ ማድረግ ያለበት ነው። የሰው ልጅ ዕድል ሁሉ በነጻ ንግድና በነጻ ገበያ አማካይነት ብቻ ነው የሚወሰነው። በተጨማሪም እያንዳንዱ አገር ባለው የጥሬ ሀብት አማካይነት ብቻ ነው ኢኮኖሚያዊ ዕድገትና ሊጎናጸፍ የሚችለው። ስለሆነም በዓለም አቀፋዊ የስራ ክፍፍል መሰረት ለምሳሌ አፍሪካ ለዓለም ገበያ የጥሬ ሀብት ብቻ ነው ማቅረብ ያለባት። በዚህ አማካይነት ብቻ ነው ዕድገትን ልትጎናጸፍ የምትችለው። ይህንን ርዕዮተ-ዓለም ተግባራዊ ለማድረግ ደግሞ እንደ አይ ኤም ኤፍ፣ እንደ ዓለም ባንክና እንደ ዓለም የንግድ ድርጅት ተቋቋመዋል። በነሱ አማካሪነትና ገፋፊነት አፍሪካና ሌሎች የሶስተኛው ዓለም አገሮች በራቸውን ክፍት ማድረግ አለባቸው። ይህ ዐይነቱ ምክር እያደገ መጥቶ ከ1980ዎቹ መጀመሪያ አንስቶ ብዙ የአፍሪካ አገሮች የተቅዋም ማስተካከያ ወይም የኒዎ-የኒዎ ሊበራል ኢኮኖሚክ ፖሊሲን ተግባራዊ በማድረግ፣ በአንድ በኩል በዕዳ ሲተበተቡ፣ የውጭ ዕቃ ማረጋፊያ ሲሆኑና በተወሰነ ምርት ላይ ሲረባረቡ፣ በሌላ ወገን ደግሞ ወደ ውስጥ ኢኮኖሚያቸው የባሰውን እንዲደቅ፣ ድህነት እንዲስፋፋና በዚያው መጠንም በደሀና በሀብታም መሀከል  ያለው ለዩነት የባሰውን እንዲሰፋ ሆኗል። ብዙ ጥናቶችም እንደሚያመለክቱት እንደዚህ ዐይነቱ ፖሊሲ ሆን ብሎ እንደተዘጋጀና መሪዎችና የተቀረውንም ኤሊት ዐይኑን ጨፍኖ እንዲቀበለው ተደረጓል። ክሪቲካል አመለካከት ያላቸው ምሁራን እንደሚሉን ከሆኑ ብዙዎች የአፍሪካ ኤሊቶች የተወሳሰበውን የካፒታሊስቱን ሞዴል ያልገባቸው ብቻ ሳይሆን፣ በኔዎ-ሊበራሊዝም ሽፋን ስር የሚተበተበውን ተንኮል ለመረዳት አልቻሉም ነው የሚሉን። እነዚህ ምሁራንም በትክክል እንደሚነግሩን፣ በአፍሪካ ምድር ውስጥ ዕውነተኛና ሰፋ ያለ የምሁር እንቅስቃሴ ሊዳብር አልቻልም ፤ በዚህም ምክንያት ዕውነትን ከውሸት በዲያሌክቲክ መነጽር መለየት አይችሉም የሚል ነው። ስለሆነም የአፍሪካን ኤሊት ለማወናበድና የአፍሪካን ህዝብ ኑሮ በየጊዜው በሚወጡ ሞዴሎችና ፖሊሲዎች ህይወታቸው ትርጉም እንዳይኖረው ማድረግ ይቻላል። እንግዲህ አንድ አገር በኢኮኖሚ ራሷን ካልቻለች፣ የሳይንስና የቴክኖሎጂም ባለቤት መሆን ዕድል ከሌላት እንዴት ዲሞክራሲያዊን ስርዓት ልትገነባ ትችላለች? የምዕራቡስ ዓለም በሆነው ባልሆነው አሻጥር የሚሰራ ከሆነ እንዴትስ የዲሞክራሲ ስርዓት አጋዥ ሊሆን ይችላል? የማይገባኝ ሎጂክ!

የስድሳ ዐመቱን የአሜሪካንንም ሆነ የምዕራብ አውሮፓን የውጭ ፖለቲካ ለተከታተለ በአፍሪካና በላቲን አሜሪካ ምድር በኮሙኒዝም ስም እያሳበቡ ጣልቃ መግባትና በኩዴታ አማካይነት ለነሱ የሚስማማ ሰው ስልጣን ላይ በማውጣት ዲሞክራሲያዊና ምሁራዊ እንቅስቃሴ እንዳይኖር ማገድ ነው። ከኮንጎ ዛየር ሞቡቱ እስከ ዩጋንዳው ኢዲያሚን ድረስ የተደረገው የመንግስት ግልበጣ የሚያረጋግጠው በነዚህ አምባገነኖች አማካይነት ከውስጥ ዲሞክራሲያዊ ስርዓት እንዳያብብና ራሱን ያወቀና በራሱ የሚተማመን ከበርቴያዊ መደብ ብቅ እንዳይል ለማድረግ የተካሄደ ትግል ነው። በተለይም በመንግስት የስለላ አፓራተስ ውስጥ ሰላዮችን በማስቀመጥና በቢሮክራሲው ውስጥ ለነሱ የሚስማማ ፖሊስ አውጭ በማፍራት ወይም እንዲገባ በማድረግ አጠቃላዩ የመንግስት ፖሊሲ እንዲኮላሽ ያደርጋሉ። የማይሆን ምክር በመስጠትም ሆነ በማስገደድ ወደ ውስጥ ያተኮረ ዕድገት እንዳይካሄድ ያደርጋሉ። በራሱ በሲ አይ ኤ ሰው በጆን ፐረኪን የተደረሰው Confession of an Economic Hit Men የሚባለው መጽሀፍ ይህንን የምዕራቡን ተንኮል ነው የሚያጋልጠው። ሌሎችም አያሌ መጽሀፎችና ማረጋገጫዎች አሉ። ከብራዚልና እስከቺሌ እንዲያም ሲል እስከ አርጀንቲና ድረስ በስድሳኛውና በሰባኛው ዓ.ም ኮሙኒዝምን ለመዋጋት በሚል የተካሄደው ዘመቻና የመንግስት ግልበጣ በእርግጥም ኩሙኒዝምን ለመዋጋት ሳይሆን በእነዚህ አገሮች የኢንዱስትሪ አብዮት እንዳይካሄድና የከበርቴ መደብ ብቅ እንዳይል ለማድረግ ነው። ሰለሆነም በአሜሪካን የሚሊታሪ ሳይንስና በሚልተን ፍሪድማን ኢኮኖሚ የሰለጠኑ ሰዎች ስልጣንን እንዲቀዳጁ በማድረግ ህብረተሰቡን

ማከረባበት ገቡ። ፋሺስታዊ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ተግባራዊ በማድረግ የአሜሪካንን የፊናንስ ኦሊጋርኪ ጥቅም ተግባራዊ ማድረግ ቻሉ። እነዚህን አገሮች በዕዳ በመተብተብና አንጀት አጥብቅ የሞኔተሪ ፖሊሲ ተግባራዊ እንዲሆን በማድረግ፣ በአንድ በኩል በወለድና የወለድ ወለድ ክፍያ አማካይነት ሀብት ወደውጭ እንዲወጣ አደረጉ፣ በሌላ ወገን ደግሞ በኢንዱስትሪዎች መዳከም የተነሳ የአገር ውስጥ ገበያ እንዳያድግ ሆነ። የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም በላቲን አሜሪካ የፈጸመውን ወንጀል በሚመለከት ብዙ የአሜሪካ ምሁራን በሰፊው ጽፈዋል። የነሱን መጽሀፍ ላገላበጠና ሁኔታውን በጥብቅ ለተከታተለ በቂ ማስርጃ ሊያገኝ ይችላል። ከሃምሳኛው ዓ.ም ጀምሮ ሲአይ ኤ ለአሜሪካን የማይስማሙ ሰዎችን በመግደልና ውሸት በማውራት የሚያደርገውን ወረራ በዶኩሜንተሪ ፊልም ተዘጋጅቶ ታይቷል። በአገራችንም በአፄ ሃይለ ስላሴ ዘመን የተካሄደው ትግል ከላይኛው ጋር ሲመዛዘን የሚያንስ ቢመስልም ዋናው ዓላማው ኢትዮጵያን አቀጭጮ ማስቀረት ነው። በደርግ ላይም የተካሂደው ዘመቻ የምዕራቡ ዓለም ሊያሳምነን እንደሚሞከረው ኮሙኒዝምን በእንጭጩ ለመቅጨት ሳይሆን ብሄራዊና የአንድነት ስሜት እንዳይዳብር ለማድረግ ነው። የኛ የምዕራቡን ካፒታሊስት ተንኮል አለመገንዘብና በትናንሽ ነገሮች መደለል፣ በተለይም ለአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም መሳሪያ እንድንሆን አድርጎናል። ጠለቅ ያለና የሾለ ምሁራዊ አስተሳሰብ ለማዳበር ባለመቻላችን ርስ በራሳችን እንድንጨራረስና የአሜሪካን መሳሪያ ለመሆን በቅተናል። በተለይም በርዕዮተ-ዓለም ሽፋን ስም የተካሄደበን ዘመቻ ርስ በርስ እንድንጠራጠርና ለመጠቋቆም በቅተናል።

የሃያ ዐመቱን የኢህአዴግ ፖለቲካ እንመልከት። አሜሪካንም ሆነ የተቀሩት የምዕራብ አውሮፓ አገሮች በአገራችን ምድር በእርግጥም ዲሞክራሲያዊ ስርዓት እንዲገነባ ቢፈልጉ ኖሮ እንደዚያ ፀረ-ዲሞክራሲውያዊ ስራ ሲሰራና ህዝብን ሲከፋፍል ሲያዩ ዕርዳታ አንሰጥህም ማለት በቻሉ ነበር። በእነሱ ዕምነት ግን ወጣትና ተስፋ በሚጣልበት መሪ አማካይነት አገሪቱ ወደ ዲሞክራሲያዊ ስርዓት እያመራች ነው በሚል ያልተቆጠበ የገንዘብ፣ የማቴሪያልና የፖለቲካ ድጋፍ መስጠት ነው ሙያዬ ብለው የተያያዙት። ፀረ-ሳይንሰና ፀረ-ህዝብ የሆነውን የኒዎ-ሊበራል ፖሊሲም ከላይኛው ዕርዳታ ጋር በጥብቅ የተያያዝና በእከክልኝ ልከክልህ ፖለቲካ አማካይነት ብሄራዊ ስሜትን ለማዳከምና የተኮላሸ የህብረተሰብ ክፍል በመፍጠር በአካባቢው አገሮች የጦርነት ፖለቲካ ከማካሄድ ስሌት ጋር የተያያዘ ነው። ከአንዳንድ የዋህ ኢትዮጵያውያን የፖለቲካ ተዋንያን የሚሰጠው አስተያየት፣ ኢትዮጵያ ብትዳከምና ብትፈርስ አሜሪካ ምን ጥቅም ያገኛል? የሚለው አባባል የዓለም አቀፍ ፖለቲካን አወቃቀርና ወደ ውስጥ ደግሞ የካፒታሊስት ኢኮኖሚ በምን መልክ እንደተዋቀረ በቅጡ ካለመገንዘብ የተነሳ ነው። በተለይም ከምርጫ 1997 ዓ.ም ወዲህ አሜሪካንንም ሆነ የአውሮፓውን አንድነት ተቃዋሚው ያደረገው መለማምጥና „የዲፕሎማሲ ትግል“ ፋይዳ ሊያገኝ ያልቻለው የምንፈልገውን ነገር የሚያደርግልን ውሻ ስላለን እናንተ ከሱ ስለማትሻሉ ለስልጣን አትገቡም በማለትም ነው። ስለዚህም አንዳንድ የቅንጅት መሪዎች እኛ የምንሰጣቸውን ምክር ትተው ከነቲም ክላርክ ጋር በመታሸት የምርጭ 97 ዓ.ም ውጤት ሊከሽፍ በቃ። ሊጠራ የታቀደው ሰላማዊ ሰልፍና የቤት ውስጥ አድማ እንዲቀር የተገደደው በፈረንጆች ላይ ጭፍን ያለ ዕምነት ስለተጣለ ነው። ምርጫ 97ን ያከሸፋት እነ አቶ መለስ ሳይሆኑ ራሳቸው የቅንጅት መሪዎች ናቸው። የኢትዮጵያም ህዝብ የሚለው ቅንጅት ሳይቸግረው ምርጫ ብሎ አስጨረሰን ነው። በእርግጥ በብዙ ሺህ የሚቆጠር ወጣት ሊሸሽ ሲል ታርዷል። ሀቁ ይህ ነው። ይሁንና የተቃዋሚው ኃይል ይህ የምዕራብ አውሮፓና አሜሪካ አገርን የማዳከምና የማፈራረስ ፖለቲካ ስላልገባው በሚያሳፍር መልክ አስር ጊዜ አቤቱታውን ከማሰማት አላቋረጠም። ይህ የተቃዋሚው ፖለቲካ ዘይቤ ራሱንም ምዕራቡን አስገርሞታል። እኛ አገራችሁን እያፈራረስ ነው ከኛ ምንድነው የምተጠብቁት እስኪሉና በግልጽ እስኪናገሩ ድረስ ነው ተቃዋሚው ኃይል የሚጠባበቀው። በግልጽ አውጥተው ቢናገሩም እንኳ የተቃዋሚው ኃይል ልናምናችሁ አንችልም ብሎ በየዋህነቱ እንደሚገፋበት መጠራጠር አይቻልም። ከአንዳንዶቹ የዋሆች የሚሰነዘረው አነጋገር ደግሞ አቶ መለስ የማይሆን ኢንፎርሜሽንና ስታቲስቲክስ እየሰጣቸው ያታልላቸዋል የሚል ነው። አቶ መለስ እንኳን አሜሪካኖችንና አውሮፓውያንን ቀርቶ ያልተማረ ሰውንም ሊያታልሉ አይችሉም። ምክንያቱም የሚሰራው ስራ ስለሚታይና ራሱ የኢትዮጵያ ተጨባጩ ሁኔታ ብዙም ማረጋገጫ ስለማይሻ ነው።

ሀቁ ይህ ሆኖ ሳለ ታዲያ በምን ተዐምር ነው ኢትዮጵያ ውስጥ ልክ እንደ ግብፅና ቱኒዚያ የመሰለ ህዝባዊ እንቅስቃሴ ቢፈጠርና እነ አቶ መለስ ከስልጣን ቢባረሩ የምዕራቡ ዐለም ፊቱን ወደ አዲሱ ኃይል ሊያዞር የሚችለው? አዲሱን ኃይል እደግፋለሁ ቢልስ በምን መልክ ነው የሚደግፈው? ካለ ምንም ቅድመ-ሁኔታ ዲሞክራሲያዊ ስርዓት እንዲገነባ ያግዛል ወይ? ዕርዳታስ ይሰጣል ወይ? ይህንን ካላደረጋችሁ ዕርዳታ አልሰጥም ካለስ እንደ ወትሮው የኒዎ-ሊበራሊዝምን ኢኮኖሚክ ፖሊስ ተግባራዊ ለማድረግ ዝግጁ ናችሁ ወይ? አሜሪካ ከኢትዮጵያ እየተነሳ ሌሎች አገሮችን ላምስ ቢልስ ፈቃደኛ ሊኮን ነው ወይ? ይህ ከሆነ ደግሞ አልሸሹም ዞር እንደሚሉት አነጋገር ነው። ብዙ ያልተብራራ ነገር ስላለ ዶክተር ብርሃኑ ነጋም ሆነ የተቀሩት የግንቦት ሰባት መሪዎች ሰፊ ሀተታ እንድትሰጡን እንፈልጋለን። በጉግትም እንጠባበቃለን።

ዶክተር ብርሃኑ ነጋ የቱኒዚያውን ህዝባዊ እንቅስቃሴና የቤን ዓሊንና እንዲሁም የሙባራክን መባረር አስመልክቶ ፣ *„ለነጻነታችን በምናደርገው ትግል የዲሞክራሲያዊ አገሮች ድጋፍ ለማግኘት መሬት ላይ ያለው ሁኔታ መቀየር እንዳለበት ቱኒዚያም ግብጽም አረጋግጠውልናል። መሬት ላይ ያለው ሁኔታ ሲቀየር ደግሞ ትላንት እሹሩሩ ያሉትን አምባገነን አንስቶ ከማፍረጥ እንደማይመለሱ በመጀመሪያ ክቱኒዚያው ቤን ዓሊን ከዚያም ከግብጹ ሙባራክ የተማርነው ትልቅ ነገር ነው“* በማለት የቅጩን ይነግረናል። መሬት ላይ ያለው ሁኔታ ተቀይሯል ሲልስ ምን ማለቱ ነው? አንድ መሪስ ስለተባረረ መሬት ላይ ያለው ሁኔታ ተቀይሯል የሚያስብልስ ነገር ምንድነው ?

በመጀመሪያ መሬት ላይ ያለው ነገር መቀየር አለበት ሲባል አንድ መሪ የመባረሩ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን የመጨቆኛ መሳሪያዎች ፣ በተለይም የስለላ መዋቅሩ እንዳለ መደምሰስ አለበት። እንደሚታወቀው የስለላ መዋቅሮች ፣ በአገራችን ደግሞ የደህንነት ጥበቃ የሚባሉት ከምዕራቡ ዓለም ካለምንም ማሰብ የተወሰዱና ስልጣን ላይ ያሉትን ለመጠብቅና ከህዝብ የሚመጣውንም ብሶት በእንጭጩ ለመቅጨት የተዘጋጁ ናቸው። በተጨማሪም ክሪቲካል አመለካከት ያላቸውን ምሁራን ለማጥፋት ነው። ስለሆነም እነ ሙባራክ ቢባረሩም የስለላ መዋቅሩ እንዳለ ነው። በሲአይ ኤና በሙባራክ የስለላ መዋቅር መሀከል የጠበቀ ግኑኝነት እንዳለ የታወቀ ሲሆን ፣ ሁኔታውም በዚያው እንደሚቀጥል ግልጽ ነው። በሁለቱም አገሮች ሰሞኑን የሚታየው ሰላማዊ ሰልፍና ግብግብ የሚያረጋግጠው ሰፊው ህዝብ ፣ በተለይም ወጣቱ በሁኔታው እንዳልተደሰተ ነው። አንዳንድ የግብጽ ምሁራንም እንደሚሉት አብዮት ከሰራን ከጥቂት ቀናት በኋላ ፀረ-አብዮት እየተካሄደብን ነው የሚሉት። እንግዲህ ምኑ ላይ መሬት ላይ ያለው ሁኔታ የተቀየረው? ምናልባት ለዶክተር ብርሃኑ ነጋ የሚታየው ነገር ለኛ ላይታየን ይችል ይሆናል። ከዚህ በተረፈ በተለይም በግብፅ ሚሊታሪው ራሱ ብዙ የኢኮኖሚ ዘርፎችንም ይቆጣጠራል። ከዚህም ሌላ ጠቅላላው ሁኔታ ለአሜሪካኖችና ለምዕራብ አውሮፓ በሚስማማ መልክ እንዲደራጅ ጥድፊያ ተይዟል። አሜሪካንም ሆነ ምዕራብ አውሮፓ እነሱ በሚፈልጉት መንገድ በቻ እንዲሄድ የማታለል ስራቸውን እየሰሩ ነው። በህግ የበላይነትና በነጻ ንግድና ገበያ አሳበው እንቅስቃሴውን ለማኮላሸት ደፋና ቀና እያሉ ነው። በተለይም ከቱኒዚያ ምሁራን የሚሰማው ሮሮ ይህ የምዕራቡ ዲሞክራሲ ተንኮል ነው። በሁለቱም አገሮች ከኛ በተሻለ መልክ የዳበረ ምሁራዊ እንቅስቃሴ ቢኖርም ወደ ኢኮኖሚ ፖሊሲ ሲመጣ ትልቅ ውዥንብር አለ። ሰሞኑን ቀናና ክሪቲካል አመለካከት ካላቸው የጀርመን ምሁራን ጋር ባደረግነው የሃሳብ መለዋወጥ የደረስንበት ድምደማ ፣ እነ አይ ኤም ኤፍ እንደግና የኒዎ-ሊበራል አጀንዳቸውን ይዘው በመምጣት ድህነቱ እንዲራዘም እንደሚያደርጉ ነው። ስለሆነም ሰፊውን ህዝብ የሚጠቅም ፣ በተለይም ደግሞ ለወጣቱ የሙያ ማስልጠኛ ኢንስቲቱሽኖች መስርቶ ተስፋ እንዲኖረው ለማድረግ ግብፅም ሆነ ቱኒዚያ ብዙ ዐመታት መጠበቅ አለባቸው ማለት ነው። በተጨማሪም ኢኮኖሚው በሰፊው ሪፎርም መደረግና ህዝባዊ ተሳትፎ እንዲኖረው ለማድረግ ውስብስብ ሁኔታዎች ከበፊት ተደቅነዋል። ያገር ውስጥ ሁኔታን ትተን ፣ የዓለም አቀፍ ኮሙኒቲ የሚባለው ልክ እሱ በሚፈልገው መልክ ብቻ የኢኮኖሚክ ሪፎርም ተጠቃሚ ይሆናል። ይህም ማለት አዳዲስ ኃይሎች በመፈጠርና በመኮትኮት የግብፅንም ሆነ የቱኒዚያን ህዝቦች ህልም ዕውን ከማድረግ ይልቅ የዓለም አቀፍን የፊናንስ ኦሊጋርኪ ጥቅም ተግባራዊ ያደርጋሉ ማለት ነው። ዛሪ እንኳ

ባይሆን ሰሞኑን በግሪክ ላይ የሚደረገው ማዕቀብና አንጀት አጥብቅ የቁጠባ ፖሊሲ በሁለቱ አገሮች ተግባራዊ በመሆን የውስጥ ገበያ እንዳያድግ ይደርጋሉ ማለት ነው። ዶክተር ብርሃኑ ነጋ ቀለል አድርጎ ለማየትና ሊያዘናጋን እንደሚሞክረው ነገሩ ቀለል ተብሎ መታየት የለበትም። ምናልባትም ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውያን የተለየ ግምት አላቸው ብሎ አስቦ ይሆናል። እናንተ ምስኪን ኢትዮጵያውያን ሳናውቀው እስከዛሬ ድረስ ዲሞክራሲን ከሚጠላና ጭቆናን ከሚያስፋፋ አገዛዝ ጋር አብረን ስንሰራ ነበር ፤ ምክንያቱም ያታልለን ስለነበር ማየት የሚቻለውን ነገር ሁሉ እንዳናይ ተጋርደን ነበር ፤ ከእንግዲህ ወዲያ ከእናንተ ጎን በመቆም ሳይንስና ቴክኖሎጂን እናፈስላችኋለን ፤ ቆንጆ ቆንጆ ከተማዎችንም እንገነባላችኋለን ፤ የባቡር ሃዲድም በመዘርጋት ሰፋ ያለ የንግድ እንቅስቃሴ እንዲዳብር እናደርግለን ፤ በዚያውም የተከበረችና ጠንካራ ኢትዮጵያን እንገነባላችኋለን ፣ ብሎ ታስቦ እንደሆን በጣም የዋህነት ነው። ለማንኛውም ነገሩ እጅግ በጣም ውስብስብና በኛ መሀከልም የሚደረገው ትግል ውጣ ውረድ የበዛበት እንደሚሆን አይካድም።

ለመሆኑ ዶክተር ብርሃኑ ይህንን ዕምነት እንዴት ሊያዳብር ቻለ? እንደተከታተልኩት ከሆነ በተለይም የነጻ ገበያንና የሊበራል ርዕዮተ-ዓለምን እናራምዳለን የሚሉ ኢትዮጵያውያን ዓለምን በጥቁርና በነጭ ስለው ነው የሚመለከቱት። ሳናውቀው በብዙዎቻችንም ጭንቅላት ውስጥ አንድ የተቀረጸ ነገር አለ። ፈረንጅን እንደ አምላክ ማየት። ሊሳሳቱ ቢችሉም እንኳ መጨረሻ ላይ ወደ ቀናው መንገድ ይመጣሉ የሚል አስተሳሰብ በሁላችንም ዘንድ ያለ ይመስለኛል። እዚህ ላይ እንዲያው በደፈናው በነጭ ላይ ዘመቻ ለማካሄድ ሳይሆን ፣ በተለይም የኢኮኖሚና የፖለቲካ ኤሊቱ የሚያካሂደው ፖሊሲ ራሱን ለመጥቀም ብቻ ሳይሆን ሌሎችንንም ለማዳከም ነው። ቢያንስ ያለፈው የሁለት መቶ ዐመት ፖለቲካ ፣ በተለይም ደግሞ ባለፈው ስድሳ ዐመታት የተካሄደው ፖለቲካ የሚያረጋግጠው የምዕራቡ ዓለም ፖለቲካ ከተንኮልና አገሮችን ከማዳከም ጋር የተያያዘ ነው። በታሪክ ውስጥ ታላላቅ ጦርነቶችን አስነስቶ ለብዙ ሚሊዮን ህዝብ ዕልቂት ተጠያቂ ሊሆን የቻለው የጥቁር ፣ የላቲንና የአሲያ ህዝብ ሳይሆን አሜሪካና ምዕራብ አውሮፓ ናቸው። ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት በኋላም ቀላልና ትላልቅ ጦርነቶች ቀስቅሶ ህዝቦችን ማስጨረስና ማፈናቀል የአሜሪካና የአውሮፓ ተግባር ነው። እጅግ በረቀቀ መንገድ ዓለምን የሚያስሰውና የሚያተረማምሰው ሰለጠንኩኝ የሚለው ዓለም ነው። ትላንትናና ዛሬ በብዙ የሶስተኛው ዐለም የሚካሄዱት ጦርነቶች የውክልና ጦርነቶች ናቸው። አንዳንዶች ሊያሳምኑን እንደሚሞክሩት ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት በኋላ የተፈጠሩት ውዝግቦች ኮሙኒስቶች የፈጠሩት ሳይሆን አሚሪካኖች በሚሰሩት ተንኮል ነው። የዓለምም ኢኮኖሚ የተዋቀረው ለእነሱ በሚስማማ መልክ ነው። ኒዎ-ሊበራሊዝምና በግሎባላዜሽን ስም የሚካሄደው መስፋፋት ጥሬ ሀብቶችን ለመቆጣጠርና የየአገሮችን ኢኮኖሚዎች አዳክሞ የራስን ሸቀጥ ለማራገፍ ነው። በግሎባላይዜሽን አማካይነት ዓለም ወደ መንደርነት የተቀየርች ሳትሆን ፣ የሸቀጣ ሸቀጥ ማራገፊያና ህዝብን ማመሺያ ነው የሆነችው። ምናልባት ለአንዳንዶቻችን ሞባይል ስልክና ሌፕቶፕ ይዘን ጉድ ጉድ ስላልን የተቀረው የዓለም ህዝብ ያለፈለት ይመስለን ይሆናል። በቢሊዮን የሚቆጠር ህዝብ በድህነትና በረሃብ እንዲሁም ሌሎች መሰረታዊ ነገሮችን በማጣቱ እንዲሰቃይ የመሆኑ ጉዳይ ፣ አይ የተፈጥሮ ህግ ፣ ወይም ደግሞ የደሀው ህዝብ ጥፋትና ድክመት ተደርጎ ተወስዶ ሊሆን ይችላል ። የሰብአዊ መብቱም መገፈፋ በዓለም አቀፍ ደረጃ በተቀነባበረ መልክ ከሚካሄደው ሁኔታ ጋር ተሳስሮ ሊታይ አይችም ይሆናል። ህዝቡ በየአገሩ እንዳይኖርና ቆንጆ ቆንጆ ነገሮች እንዳይሰራ መታገዱም የየአገሩ ኤሊት ተግባር ብቻ ተድርጎ ተውስዶም ሊሆን ይችላል። የሶስተኛው ዓለም መንግስታትና ኢንስቲቱሽኖች የካፒታሊስቱን የምዕራብ አውሮፓና አሜሪካ የሚያግዙና የሚያጠናክሩ እንጂ ወደ ውስጥ ጥሩ ጥሩ ነገሮች እንዲሰሩ ለማድረግ አይደለም የተዋቀሩት። ይህን የመሰለውን እጅግ በተሰበጣጠረ መልክ የሚካሄደውን ጭቆናና ደሀ አገሮችን ማዳከምን ነው ዶክተር ብርሃኑም ሆነ ሌሎች የሊበራል ዲሞክራቲክ አራማጆች ሊገነዘቡ የማይችሉት። ምክንያቱም ቀላል ነው። አስተሳሰባቸው ኢምፐሬሲስታዊ ስለሆነ!

እነ ዶክተር ብርሃኑ ነጋና ሌሎች የነጻ ገበያና የሊበራል ዲሞክራሲ አራማጆች ይህንን ነው ለማየት የማፈልጉትና የማይችሉት። ፕላቶን እንደሚያስተምረን መታየት

የማይችለውን ነገር ማየት የማይችሉ ብቻ ሳይሆኑ ፣ ጠለቅ ብለው በመሄድ የነገሮችን አነሳስ ፣ ዕድገትና አቅጣጫ ለመመርመር የማይፈልጉም ናቸው። በተሰበጣጠረው በማይክሮና በማክሮ ኮስሞስ መሀከል ያለውን የተዋሰሰበ ግኑኝነት ለመረዳት በፍጹም አይችሉም። ብዞዎችም በመሳፍንቶች ዘንድ ከሚካሄድ ውይይት አልፈው ህዝባዊ ብሶቶች በሚነሱባቸው ትላልቅ ሰሚናሮች ጋ በመካፈል ትችታዊ ውይይትንና አመለካከትን ለማዳበር ዝግጁ አይደሉም። የብዞዎቹ የሊበራል ዲሞክራሲ አራማጅ ነን ባዮች ችግር ከዚህ የካፒታሊስት ኒዎ-ሊበራል አቀንቃኞች ካዋቀሩት ቲዎሪ ባሻገር ርቀው ሂደው ለማየት አለመቻል ነው። በተለይም የትምህርት ቤት ኢኮኖሚክስንና የዕድገት ኢኮኖሚክስን አስመልክቶ የታወቁት ስዊዲናዊ ኢኮኖሚስትና በሰላሳኛው ክፍለ-ዘመንም ሆነ ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት በኋላ የስዊድንን ኢኮኖሚ መስመር እንዲይዝ ያደረጉት ኢኮኖሚስት ፕሮፌሰር ጉናር ምርያልድ ማስጠንቀቂያ ሰጠተው ነበር። አሳሳች መሆኑን በዝርዝር አረጋግጠዋል። ሌሎችም እንደ ፕሮፌሰር ኤሪክ ራይነርት እጅግ ግሩም በሆነ መጽሀፋቸው ፣ *„ለምን ደሀ አገሮች ደሀ ሆነው ቀሩ ፣ እንዴትስ ሀብታም ሀገሮች ሀብታም ሊሆኑ በቁ“* በሚለው መጽፋቸው በየትምህርት ቤት የሚሰጠውን የኢኮኖሚክስ ትምህርት አጥብቀው ያወግዛሉ። በብዙ መቶ ሺህ የሚቆጠሩ ኢኮኖሚስቶች በዚህ መልክ ተኮትክተው አውቀውም ሆነ ሳያውቁ ለዓለም ድህነት አስተዋፅዖ እንዳደረጉ ያመለክታሉ። ሌሎችም ክሪቲካል አመለካከት ያላቸው ምሁራን ይህንን የፕሮፌሰር ምይራልድንና ፕሮፌሰር ራይነርትን ትንተናና ሳይንሳዊ ማስረጃ ትክክል መሆኑን ያረጋግጣሉ። ለንደን የሚገኘው ስኩል ኦፍ ኦሪዬንታል ስተዲስ(School of oriental studies)የኒዎ-ሊበራልን ፖሊሲም ሆነ ቲዎሪ ፣ በቲዎሪና በኢምፔሪካል ደረጃ በማሳየት አሳሳችነቱን ያረጋግጣል። ብዙ ፕሮፌሰሮችም በግልጽ ትግል በማድረግ አዲሱ ትውልድ ትክክለኛውን መንገድ እንዲይዝ ጥረት እያደረጉ ነው። በኛ ምሁራን ጋ ያለው ችግር ግን ይህንን በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚካሄደውን ትግል እንዳለዩ አድርጎ ማለፍና ካለ ኒዎ-ሊበራል ፖሊሲና ከነጻ ገበያ ሌላ መፍትሄ የለም ብሎ ቁጭ ማለትና ሌላውን ደግሞ እንደ ዕብድ ማየት ነው። ይህ አጉል ትልቅ ሰዎች ነን ብለው አንዳንድ ሰዎች የማያካሂዱት ትግል ለንቃተ-ህሊና ማደግና ለስለጣኔ እንቅፋት ሆኗል ማለት ይቻላል። በዚህ መልክ የሚካሄድ ትግል እጅግ የመረረና የድህነቱንም ዘመን የሚያራዝም ነው። ስለሆነም በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ተሳስተዋል። ይህንን ሁኔታ የመግታቱና ቀናውን መንገድ የማያያዙ ጉዳይ በብዙ ሰዎች ትከሻ ላይ መውደቅ አለበት። ይህ ሲሆን ብቻ ትግሉ ፍሬያማ ይሆናል። ካለበለዚያ ግን የሰለጠነችና የተከበረች ኢትዮጵያን ማየት ሳንችል እናልፋለን ማለት ነው።መልካም ንባብ !

**ፈቃዱ በቀለ**

fekadubekele@gmx.de

<u>ማሳሳቢያ ፣</u>

1. ይህ ጽሁፍ በምንም ዐይነት የዶክተር ብርሃኑን ሃሞት ለመግደል የወጣ ጽሁፍ ሳይሆን የቱን ያህል የአቋም ልዩነት እንዳለን ለማመልከት ነው።
2. እስካሁን ድረስ ዶክተር ብርሃኑ ነጋ ስለተቅዋም ፕሮግራምና(Structural Adjustment Program) የኒዎ-ሊበራል ፖሊሲን በሚመለከትና በአገራችን ምድር ውስጥ ተግባራዊ ከሆነ ወዲህ ፖሊሲው የፈጠረውን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ቀውስ አንስቶ አላወያየንም። ለዲሞክራሲና ነጻነት እታገላለሁ የሚል በእንደዚህ ዐይነት አገር አፍራሽ ፖሊሲ ላይ አቋሙን ግልጽ ማድረግ አለበት። የብዙዎቹ ተቃዋሚ ነን የሚሉ ድርጅቶችም ድክመት እዚህ ላይ ነው።
3. ወደፊት ካለምንም ፍርሃት የተቃዋሚውን ድክመት ከሳይንስ አንፃር እየተነተኑ ማቅረብ የአገር ወዳጆች ተግባር መሆን አለበት። በአውሮፓ ውስጥ የተደረገው ህብረ-ብሄርንና ጠንካራ ኢኮኖሚን የመገንባቱ ትግል በሆያ ሆዬ ላይ ተመስርቶ ሳይሆን ፣ ሳይንሳዊ ትግልን መሰረት በማድረግና በግልጽ በመወያየትና በመከራከር

ነው። ከዚህ ውጭ እታገላለሁ ማለት ድህነቱን ማራዘምና ስልጣኔ እንዳይመጣ ጥረት ከማድረግ ውጭ ተነጥሎ ሊታይ በፍጹም አይችልም።